December 23/2020

ጉዳዩ፤ ከቀድሞው አግ7 ለኢሳት የተሰጠ የገንዘብ ብድርን ይመለከታል፤

ባለፉት በርካታ ዓመታት የኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ድርጅት ከአግ7 በግልፅም ሆነ በጥቂት አመራሮች እውቅና የተለያዩ ድጋፎችን ሲያገኝ መቆየቱ የምታወቅ ነው:: ኢሳትም ለበርካታ ዓመታት እራሱን ችሎ መንቀሳቀስ መቻሉ የሚደነቅ ቢሆንም በየጊዜው ከገንዘብ እጥረት የተነሳ የሳተላይት ክፍያዎችን ለማድረግ ድጋፍ ሲጠይቅም ቆይቶዋል:: አግ7ም የኢሳት ህልውና ያሳስበው ስለነበርና ድርጅቱ እራሱን ችሎ መልሶ መክፈል የሚችልበት አቅም ላይ እስከሚደርስ በሚል ስምምነት በብድር መልክ የተሰጠው ገንዘብ $181,650 ዶላር እስከአሁን ክፍያው አልተጀመረም::
በመስከረም 2019 ከዶ/ር አዲሱና ዶ/ር አዚዝ ጋር በነበረን ስምምነት መሰረት እንዲሁም አክቶበር 28/2019 በተለዋወጥነው ኢሜይል ላይ እንደተያያዘው የክፍያ ሰነድ መሰረትም ከጃንዋሪ 2020 በአነስተኛ ወርሃዊ ክፍያ እንደሚጀመርና በኢሳት የሂሳብ ሰነድ/መዝገብ ላይም ይህ ብድር እንደሚካተት ስምምነት ላይ መድረሳችን ይታወሳል። ይህ በብድር የተወሰደው ገንዘብ በኢሳት የሂሳብ ሰነድ እንደሚካተት ሙሉ እምነት ቢኖረኝም፤ በነበረው የኢሳት የገቢ እጥረት ምክንያት ክፍያው ግን እስከአሁን ሳይጀመር ቆይቶዋል። አግ7 እራሱን ሲያከስም ያለውን ንብረት ለሚመሰረተው አዲሱ ፓርቲ እንዲያስተላልፍ በጠቅላላ ጉባኤ አዲስ አበባ ላይ ሲወሰን ይህም ገንዘብ የዚያ አካል መሆኑ ታውቆ ነው።
ስለዚህ የኢሳት ቦርድ ለዚህ ጉዳይ ክብደት በመስጠት ክፍያውን በስምምነቱ መሰረት እንድትጀምሩና እልባት እንዲያገኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

ከምስጋና ጋር
ተስፋዬ ለታ (ሁሉቃ)

ግልባጭ፤ ዶ/ር አዲሱ መንግሻ
ዶ/ር አዚዝ መሃመድ
ፕሮፍ. ብርሃኑ ነጋ
አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ